ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ
Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity
Efdpu@aol.com www.Finote.org

*የፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ ሀተታ*
*ነሐሴ 12 ቀን 2007 ዓ.ም. የተላለፈ*

**ነሐሴ 2007 ዓም**

## ***ቋሩም ዝም መጽሐፉም ዝም***

አዳዲስ ኃስብ ማመንጩት የተሳነው ኅብረተስብ፤ ሁል ጊዜ በቆየውና ባሮጌው ጉዳይ ላይ ሲያመነዥግ ጊዜውን ያሳልፋል። ያንኑ በመደጋግም ፤ እያዘዋወረ፤ እያፍተለተለና እያውጠነጠነ ከመኖር የተሻለ አዲስ ኃሳብ ለማምጣት አልታደለም ። አሮጌውን በመቀባበል ብቻ የሚረካ ኅብረተሰብ፤ " እልፍ ሲሉ ዕልፍ እንደሚገኝ " እንኳን አይገነዘብም ። በልተውና ጠጥተው ከተገለገሉበት በኋላ እንደገና ለመገልገል የሚፈልጉትን የወረቀት ሳህንና ዋንጫ ( Recicle/ ሪሳይክል ) እያዟዟሩ መኖር፤ የፈጠራ ክኅሎትን አያበረታታም ።

አባቶችና እናቶች ባስመዘገቡት ታሪክ ብቻ እየተኮራሩ መኖር ፤ የትም እንዳላደረሰን፤ አሁን የወደቅንበት ሁኔታ በቂ ማስረጃ ሆኖብናል ። ይህ ትውልድ፤ የራሱን ችግር አስወግዶ፤ መፃዒ ዕድሉን የሚያመቻች ተግባር መፈፀም ካልቻለ፤ የአምባገነኖች ሰለባ መሆን ብቻ ሳይሆን፤ በድኅነት አረንቋ ውስጥ ተዘፍቆም ይኖራል። የዓለም ኅብረተስብ መሳቂያ መሳለቂያ ከመሆንም አይድንም። የሀገራችንም ዕድል፤ ተስፋው ብርሃን አይገኝም። ዝም አይነቅስም በመሆኑ፤ ሁሉን በዝምታ ማሳለፍ ተመርጧል ።

ሻዓቢያ ፤ በሠላም የተደላደለ ኑሮ ሲኖር የነበረውን ሕዝብ ለአመፅ እንዲነሳ የቀሰቀሰበት መፍክር ፤ " ባህላይ አይትኹን ነዐይ ይጥዐመኒ ! " እኔን ይጣመኝ ባይ አትሁን ። የሚል እንደነበር እናውቃለን ። በሀገራችን ዛሬ ስንቱ የጣመ ኑሮ እንደሚኖር ግን አናውቅም ። በመሆኑም፤ " ኑሮ፤ ጥሞኛል አትበል " ማለት አንችልም። ደስተኛ እንዳልሆነ ግን እንገነዘባለን ።

ሀገራችን ዛሬ ፤ በአስቸጋሪ ሥነልቦና ውስጥ ስለምትኖር፤ ሰው ማፍራት፤ መሪ ማውጣት፤ ሀገር ወዳድ ዜጋ መፍጠር ፤ ሕዝብ አፍቃሪ ዐርበኛ ማብቀል፤ አልተቻላትም ። አዳዲስ ሰው ማውጣቱ ቀርቶ፤ ያሉንን አዋቂዎችና ሀገር ወዳድ ታጋዮችንን እንኳ በተገቢው መንገድ ይዘን- አቅፈን -ደግፈን ልንጠቀምባቸው አልቻልንም። ይህንን ሃቅ እያንገፈገፈንም ቢሆን ልንቀበለው ይገባናል ። ምናልባት ይህንን መራራ ዕውነት መቀበል ብንችል፤ ፈጣን የአስተሳሰብ ለውጥ አምጥተን የሀገራችንን ሁኔታ ለመቀየር የሚያስችለንን ተዐምር ሥራ መስራት በቻልን ነበር። ሁሉም ነገር፤ ነበር ሆኖ እንዳይቀር ከፈልግን ፤ ይቻላል ! ይሆናል !

ይሳካል ! በሚለው ላይ ማተኮሩ ይሻለናል ፡፡ ያለዚያ፤ ላለፈው ክረምት ቤት መስራት ይሆንብናል ፡፡ ይህ ደግሞ፤

" የነበር ሲወጋ ይመስላል ያልነበር ፤

ያባታችን ጋሻ ጦር ይመክት ነበር፡፡ "

የሚል ባህላዊ ስንኝ ከመስማት የተሻለ ርባን አያስገኝም ! አዲስ ራዕይ አያመጣም ! ተስፋ መቁረጥ፤ ዙሪያ-ገደሉ የጨለመበት ኅብረ-ተስብ ነፀብራቅ ነው ለማለት ቢቻልም እንኳ፤ እንደ ከዋክብት ብሩኅ ተስፋን የሚፈነጥቁ ባለ ራዕይ ዜጎች ብቅ ብቅ ማለታቸው ግን አይቀርም ፡፡ ሀገሪቱ፤ ምንጊዜም ቢሆን፤ የወላድ መካን ሆና አታውቅም ! ወደፊትም አትሆንም !

በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ፤ በርካታ አዳዲስ ጽሀፍት በቅ ብቅ እያሉ በመውጣት ላይ ናቸው እየተባለ ይነገራል ፡፡ የአንዳንዶቹ ድርሰትም፤ ድንቅ ወደሚያሰኛቸው ተረተር እየወጣ እንደሀነ ከአንባባያን ከሚሰጡት አስተያየት መገንዘብ ተችሏል ፡፡ ይህ ተስፋ ሰጭና አበርታች ዜና ሆኗል ፡፡ ደራሲያኑን በበለጠ ሊያበረታቱ ከሚችሉት አንዱ፤ የአንባብያን መበርከት እንደሆነ ቢታሰብም፤ የዴሞክራሲ መብቶች ያለገደብ መከበር ግን ዓይነተኛውና መሠረታዊ ነው፡፡ ዴሞክራሲን፤ የወያኔ ዳፍንት አገዛዝ ባዳፈነበት ሀገር፤ ሃሳብን በነፃ የመግለጽ ዕድል የሚታሰብ ባይሆንም ቅሉ፤ ማናኛውንም አደጋ በመቋቋም የተቻላቸውን ያህል የሚሞክሩትን ደራሲያን ማበረታታትና መደገፍ የነፃነት ትግሉን ያጎለብተዋል ፡፡ ነፃነትን የቀመሰ ደግሞ በቅምሻ ብቻ አይረካም ፡፡ ለበለጠ ነፃነት ይታገላል !

ነፃ ኃሳብን የመግለጽና የማካፈል ነፃነት በታፈነበት ሀገር፤ ደራሲያንም ሆኑ አንባብያን ሊኖሩ አይችሉም ፡፡ ደራሲያኑ በኅቡዕ ( በቀድሞ ምስራቅ አውሮፓ፤ በአፍሪካ፤ በአስያና በላቲን አሜሪካ ሀገራት እንደታየው) ሊጽፉ ቢችሉም እንኳን፤ አንባባቢያን ከሌሉ፤ ዕውቀት ተድፍኖ ይቀራል፡፡ የሥነ ፅሁፍ መምህራን እንደሚያስተምሩት ደግሞ፤ መስማትንና ማንበብን፤ መናገርንና መጻፍን አቻ ለአቻ አድርገው ያስቀምጡታል ፡፡ ካልሰማህ አትናገርም፤ ካላነብብክ አትጽፍም የሚል መልዕክት ለማስተላለፍ ይመስላል ፡፡

አዲሱ ትውልድ ማነኛውንም ችግር ሁሉ እየተቋቋመ አዕምሮውን በንባብ ፤ ማጎልበትና ማበልፀግ ይጠበቅበታል፡፡ ሀገር የምትገነባው በበለፀገ አዕምሮ ብርታትና ጉልበት መሆኑ፤ ዋቤ ጥቀሱ የሚባለበት አይደለም ፡፡ " ያላነበበ አይፅፍም ፤ ያላዳመጠ አይናገርም " ነውና ፤ አዲሱ ትውልድ፤ የመጽሐፍ ቀበኛ የድንቁርና መጋኛና ደመኛ ከሆነ፤ የነገዋ ኢትዮጵያ፤ ባለ ራዕይ ዜጎች የሞሉባት ሀገር ትሆናለች፡፡

ራዕይን አንግቦ የሚራመድ ትውልድ ለሀገር/ ለወገን የተስፋ ብርሃን ሰጭ ይሆናል ፡፡ ባለ ራዕይ መሪዎችንም ለማፍራት ዕድል ያገኛል ፡፡ የሠለጠነ የሰው ኃይል ምንጮች፤ ትምትህርት/ንባብ/ መፃህፍት ናቸው፡፡ ደራሲያንን የሚያበረታታና የሚያበረክት የአንባቢ ብዛትና ትጋት እንደመሆኑ፤ ደራሲያንና አንባብያን አቅኝና ሸማች በመሆን ከተባበሩ ፤ ሀገሪቱ የሊህቃን- የምሁራን- የጠቢባን- ማዕከል ትሆናለች ፡፡

በአንፃሩ፤ ኢትዮጵያ፤ ደናቁርት መሪዎች ፤ በላዒ-ሰብ ጉግማንጉጎች፤ ፍርደ- ገምድል ጲላጦሶችና ከሃዲያን ይሁዳዎች ፤ የሚጫወቱባት ሀገር ልትሆን አትችልም ።

የራሷ ፊደላት- ልሣናት፤ ስንክሳር- መዛግብት፤ መፃፍት- ሊቃውንት ፤ ዜማና ሙዚቃ፤ ለደስታው እስክስታ፤ ለሀዘኑ እርግዶ፤ ለሰርጉ ዳንኪራ ፤ ለውጊያው ቀረርቶ፤ ለጦርነቱ ፤ ነጋሪት- ዕምቢልታ ፤ የሀገራችን ጠበብና ሥልጣኔ ቅርስ ሆነው ቆይተዋል ። ሁሉም ሲጠቃለሉ፤ የሀገራችን ሥልጣኔ ድምር ውጤት ነበሩ፡፡ አሁንም ናቸው ። የዚህ ታሪክና ሥልጣኔ ባለቤት የሆነ ሕዝብ ራዕይ ያለው መሪ፤ ሊያወጣ ይገባው ነበር ። ያ ግን አልሆነም ። እየመጣ የሚሄደው " መሪ" ሁሉ ፤ ለነገ ራዕይ ስላልነበረው፤ "የኋላ ልጅ ይጨነቅበት ! " ብሎ ይጠፋል ። እዳው ለተተኪው ትውልድ ይተርፋል ።

" የወለዱትን የማይስሙለት፤ የጻፉትን የማያነቡለት፤ የደገሱትን የማይበሉለት " ኅብረተሰብ፤ እንደ ዉሊታ ቢስ ይቆጠራል ። የደራሲያን መኖር አንባብያንን ካላፈራ፤ አንባቢውም፤ የደራሲያኑን ዋጋና ጥቅም ካልተረዳ ፤ ዕውቀትና ጥበብ ተለያይተው ይቀራሉ። የሁሉም ቆልፍ ጥያቄ ግን ፤ የዴሞክራሲ ሥርዓት መስፈን መሆኑ የሚያከራክር አይደለም ። የዴሞክራሲ አስተዳደር ከሌለ ደግሞ ምኞቱና ተስፋው ሁሉ፤ የበረሃ ንብልብሊት ( The Desert Mirage ) ሆኖ ይቀራል ።

ዛሬ በሀገራችን የዴሞክራሲ መብት ቀርቶ፤ ጭላንጭሉ እንኳን ደብዛው ጠፍቷል። በቅርቡ ኢትዮጵያን የጎበኙ አንድ የውጭ ሀገር መሪ፤ ወያኔ የቀለደበትን ምርጫ ፤ " ዴሚክራሲያዊ ነው " ማለታቸው፤ እኛን ኢትዮጵያውያንን ቀርቶ፤ መላውን ዓለም አስገርሞታል ። እኚህ ሰው፤ ያሻቸውን ለመናገር የራሳቸው ጉዳይ ቢሆንም፤ የሕዝባችንን የማሰብ ችሎታ፤ ( Intelligence ) መናቃቸው ግን አናድዶናል ። በማያውቁትና ባልተረዱት የሀገራችን ጉዳይ መግባታቸው ትዝብት ላይ ጥሏቸዋል ።

የፕሬዝደንቱን ምፀት ፤ " የዐይጥ ምስክር ድንቢጥ " ነች ከሚለው ብሂል በላይ አሻግረን ልናስብበት ይገባናል ። በሀገራችን ዛሬ፤ የመጻፍና ሃሳብንም በአደባባይ በነፃ የመግለፅ መብት እንደሌለ እያወቅን፤ ማንም አልፎ- ሃጅ መጥቶ ሊያታልለን መሞከሩ ባልተገባው ነበር ። ኢትዮጵያውያን " ብኩርናቸውን በጭብጥ ምስር መለወጥ " ልምድ ስለሌላቸው፤ ነፃነታቸውን የሚግፍፍ ርዳታ፤ በአፍንጫችን ይውጣ ባዮች ናቸው። ኩራት ራት ነውና፤ አዋርዶ ከሚመጣ ርዳታ፤ ሽህ ጊዜ ነፃነትን ከድህነት ጋር መምረጥ ይበልጣል ።

ማንም ባዕድ ኢትዮጵያን እንዲወድ ባይጠበቅም፤ የህዝቡን የማሰብ ችሎታ ግን ሊፈታተን አይገባውም ። አይፈቀድለትምም ! ባዕዳኑ ባይወዱንም እንኳ ሊጠሉን ባልተገባቸውም ነበር ። " እንኳን ሲሸጡኝ ሲስማሙብኝ " አውቃለሁ እንዲሉ፤ ማንም ሲያስነጥሰው፤ ጉንፋን ከማያዙ በፊት የምንረዳ ሕዝቦች ነን ።

በባኅላዊ ልምድ ላይ የተመሰረተ ህይወት መምራት በራሱ ፤  አዲስ ኃሳብን ለማፍለቅ እንቅፋት ሊሆን እንዳማይችል፤ ታሪካቸውን አክብረውና ባኅላቸውን ጠብቀው በሥልጣኔ የተራመዱ በርካታ ህዝቦች እንደ አርዓያ ይጠቀሳሉ ። በአካባቢያቸው የዴሞክራሲ ተምሰሌት ናቸው ተብሎ የሚነገርላቸው፤ ሕንድና ጃፓን እንደ ማስረጃ ይቀርባሉ ። ሁለቱም በዕድገት ደረጃ፤ የት እንደ ደረሱ ሁሉም የሚያውቀው ሃቅ ነው ።

የጃፓንን የሥልጣኔ ዕድገትና ርምጃ ቀደም ብለው የተገነዘቡ ኢትዮጵያውያን ምሁራን ከጃፓኖች ተመክሮ፤ ብዙ ጠቃሚ ብልሃቶች እንደሚገኙ መናገራቸው ተደጋግሞ ሲነገር እንደነበር ይታወቃል።  ጃፓንን እንደ ሞዴል ለማየት አስፈላጊ የነበረው፤ ባህሏንና ታሪኳን  ጠብቃ ፤ ነፃነቷንና ሀገራዊ ሉዓላዊነቷንም አስከብራ በሥልጣኔ  የተራመደች  ሀገር በመሆኗ እንድሆነ ይጠቀሳል  ።ሀገራችንም ቢሆን፤ ይህንን ርምጃ ለማድረግ የሚሳናት እንዳልነበረች፤ በፀፀት እየተናገሩ ያለፉ በርካታ ሀገር-ወዳድ ዜጎች ነበሩ ።  ይህንን በመገንዘብ፤ ከአምሳ ዓመት በፊት አንድ ድምፃዊ ተጫዋች ፡-

" ለምሳሌ ጃፓን በጣም  ሥልጡን ናቸው ፤

አልተቀላቀለም ከሌላ ባኅላቸው ።  "

እያለ ሲያቀነቅን  እንደነበረ፤ የዚያ ሀገር- ወዳድ ትውልድ  የተስፋ ትዝታው ነበር።  ተስፋው ወደ ዕውን መለወጡ ቀርቶ፤ እንዲያውም ዛሬ  ይባስ ተብሎ ፤  በኢትዮጵያ መኖር /  አለመኖር ላይ ዋይታና ጨኸት ማሰማት  ሆኖ ቀርቷል ።

ዛሬ፤  ሁሉም ፤ ተስፋው እየጨለመ፤ ምኞቱ እየተነነ ፤ ራዕዩ  እየበነነ፤  ደብዛው ሳይቀር   እየጠፋ ነው ። በዚህ ምክንያት፤  ሀገርና ሕዝብ  አሳቢና - ሰብሳቢ  አጥተው ቀርተዋል።  ኅልውናው በጥያቄ ውስጥ የሚዋልል ሕዝብ ፤ ራሱ ምን እንደሚገጥመው እንኳ ማወቅ አይችልም። በደህናው ጊዜ ያላፈሩት ሰው ደግሞ በጭንቅ ቀን ተፈልጎ የሚያገኙቱ አይሆንም ። እኔ አለሁ ብሎ ብቅ ቢልም እንኳ ፤ ከመንግሥቱ ሃይለማርያም የተሻለ ስብዕና ያለው ሊሆን አይችልም ። " የገበያን ግርግር ሌባ እንደሚጠቅምበት " ሁሉ፤ ማኅበራዊ ቀውስ በሚፈጠርበት  ጊዜ፤ ለሥልጣን ያቆበቆበው ሁሉ፤ በየጎጡና ማጀቱ፤ ብቅ ብቅ ማለቱ አይቀርም  ። "የቁርጥ ቀን ልጅ ! የታሪክ አደራ የጣለብኝ ! "  የሚል አታላይ መፈክር እያሸጎደጎደ  ቲያትሩን ይሰራል ።

ደርግ፤ በዐብዮት ስም ፤ " የፖለቲካ ርምጃና ውሳኔ "  በሚል ፈሊጥ፤ ሀገሪቱን እምን ላይ ጥሏት እንደሄደ ማን ይዘነገዋል ?  ወያኔም በበኩሉ፤  በትግራይ ሕዝብ ነፃነት ስም ፤ ምን ዓይነት ወንጀል እንደሰራ/ እንደሚሰራ፤ ሕዝብ ያወቀው ታሪክ የመዘገበው ሀቅ  ሆኗል ።  ታዲያ ይህንን ሁሉ የታዘበ ሕዝብ፤ አዲስ የሚመጣውን ቢጠራጠር  ማን ይፈርድበታል ?  ለነገሩማ፤ እንደ ይሁዳ ከሃዲ ከመሆን ፤ እንደ ቶማስ ተጠራጣሪ መሆን አይሻልም እንዴ ?

ለትዝብት ያልታከተው የኢትዮጵያ ሕዝብም ፡-

" ዐይኔ ጉድ ዐዬ፤ ዕድሜየም ረዝሞ፤  ያ ዘመኔ በዝቶ ፤

ጉግ ማንጉ ሄዶ፤ ጭራቁ ሲተካ፤ ደህና ሰውም ጠፍቶ ! "

እያለ ማልቀሱን ይቀጥላል። እምባውን እንደ ጎርፍ ቢያጎርፈውም፤ ጨኸቱንም ላንቃው እስኪሰነጠቅ ቢለቀውም ሰሚ አላገኘም። " እርስ በርሳቸው የተከፋፈሉ አባላትን ያቀፈ ሀገርና መንግሥት አይፀናም " እንደተባለው፤ የተከፋፈለ ኅብረተ-ሰብም እንዲሁ ሊፀና አይችልም ። ሊፀናም ከቶ አይታደለም ። የራሳችንን ኃይል አሰባስበን፤ የራሳችንን ትግል መርተን / አካሂደን፤ የራሳችንን ነፃነት ማስበከር አቅቶን፤ ባዕድ መጥቶ እንዲረዳን እንጠብቃለን። ይህ እንዳማይሆን ግን አሁንም የተረዳን አይመስልም። ኢትዮጵያን ያጠፉ ጠላት፤ ይረዳናል ብሎ መጎናበስ፤ የውርደት ውርድት መሆኑን፤ ማወቅ በተገባ ነበር። ይህንን ማወቅ ካልተቻለ ደግሞ፤ ቢያንስ፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ የማሰብ ችሎታና የፍርድ ሚዛን ማክበር ግዴታ ነው ።

" አባማ መጥቶ ችግራችን አይቷል፤

እንደተመለሰ ቶሎ ይፈታልናል "

እያልን ራሳችንን ማተታለል ይቅርብን። ይልቁንስ፤

" ወያኔና አባማ፤ እንዴት ተቀናጡ፤ ምንኛስ ቀለዱ፤

በምኒልክ ግቢ ዳንኪራ ጨፍረው፤ እስክስታ ወረዱ፤

በሀገራችን ችግር መመፃደቃቸው፤ በሕዝባችን እምባ መዘባበታቸው፤

እነርሱ ምን ያርጉ ጥፋቱ ከኛው ነው፤ ቤታችንን ከፍተን ስንተውላቸው ! "

ለካ ትንቢት ኖሯል ቀድሞ መነገሩ፤ ጥንትም መበሰሩ፤

" ከፍት ይዋል ከፍት ይደር ብለው ሲመርቁ ፤

ቤቱም ከፍቱን ቀረ ሰዎቹም አለቁ ! "

ብለን በመቆጨት፤ ኢትዮጵያዊ ማንነታችንን በተግባር ማስመስከር ይጠበቅብናል ። ይህ ካልሆነ ግን፤ የአዞ እምባ ከማፍሰስ አያልፍም ! የአዞ እምባ የሚያለቅስልን ግን አናጣም ፤ የሚጠቅም ከሆነ ?

በ1933 ዓም ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ልክ ከስደት እንደተመለሱ ፤ በአርበኞች በኩል ፤ አንድ የምፀት ስንኝ ተነግሮ ነበር የይባላል ። ይኸውም

" እንግሊዝ እናቱ አማሪካ አባቱ ፤

ደጋግፈው አስገቡት ከቤተ መንግሥቱ "

ልብ ያለህ ልብ ብል ! ልብ የሌለህ ልብ ግዛ ! እንደ ጲላጦስ እጅን ቢታጠቡት፤ እንደ ይሁዳ የክኅደት አሳሳም ቢስሙት፤ እንደ ባንዳ ጥብቆ ቢቀያይሩት ፤ ከደሙ ንፁህ ነኝ ማለት አይቻልም። ከወንጀልም ክስ ነፃ አያወጣም !

" የፖለቲካ ሳይንስ አጥንቶ የመጣ፤

ሀገሩን ያወጣል ከነአጼው ጣጣ " ሲል የነበረው ሁሉ፤ በ 11ኛው ሰዓት ወደ ዘሩ ፤ ነገዱና ወደ ብሄሩ እያፈተለከ መሄዱን ታዝበናል ። መቆየት መልካም ነው ብዙ ያስተዛዝባል! በዚህ ምክንያት :-

" እዚህ መጥተሽ በላሽ፤ እዚያም ሄደሽ በላሽ ፤

ሰው ታዘበሽ እንጅ ሆድሽን መቼ ሞላሽ ? "

ለማለት በቅተናል ። የቆየ ሰው መልካም !

ኢትዮጵያ ከ 1933 እስከ 1966 ዓም ድረስ በምን ሁኔታ ላይ እንደነበረች የቅርብ ትዝታ ስለሆነ፤ በዚያ ላይ ማተኩርን አንመርጥም። ህይወት ዘወተር በማያቋርጥ የለውጥ እንቅስቃሴ ሂደት መገኘቷን የማይረዱ ራዕይ-ቢስ መሪዎች፤ እራሳቸው ጠፍተው፤ ሀገሪቱንም ለጥፋት ዳርገዋት ይሄዳሉ። መከራውና ፍዳው ግን ለትውልድ ይተላለፋል ።

ይህ ተደጋጋሚ ችግር እንዳይከሰት ከተፈለገ፤ ራዕይ ያላቸው ዜጎች ስትራተጂያዊ ዓላማቸውን አስተባብረው መስራት ይጠበቅባቸዋል ። አሁን እንደሚታየው ከሆነ ግን፤ እንኳንስ በስትራተጅ ( ወደ ግባችን በሚወስደን ረጅም መንገድ ) ላይ መስማማት ይቅርና በታክቲክ (በስልት) ላይም ቢሆን መስማማት የሚቻል አልሆነም ።

በአሁን ዘመን ፤ ማንም ሀገር፤ የሌላውን ሀገር ችግር ሊፈታ ቀርቶ ፤ ሊቀርፍ እንኳን አይችልም። ደንታም አይሰጠውም ። ይልቁንም፤ የራሱን ጥቅም ለማስጠበቅ ሲል፤ ከአምበገነኖች ጋር ተመሳጥሮ፤ ሕዝብ የሚጎዳ ተግባር ለመፈፀም ወደ ኋላ አይልም። ይህንን ሃቅ አበክሮ የተገነዘበ ሕዝብ፤ ሊኖረው የሚችለው ምርጫ አንድ ብቻ ይሆናል። እራሱን አደራጅቶ፤ እራሱ ታግሎ፤ ራሱን ከችግር ማውጣት እንዳለበት ለአፍታም ቢሆን ከኅሊናው ሊፍቀው አይገባም ። ያለዚያ፤ ሁሉም ነገር ፤ " ቁሱም ዝም መጽሐፉ ዝም " ሆኖ ይቀራል ! የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ ፤ ዕርምህን እያወጣህ ትግልህን ቀጥል !

ኢትዮጵያ በነፃነቷ ለዘለዓለም ትኖራለች !